የስሜት ሕዋሳቶቻችን ይነቃቁ!


* የተለያዩ ካርቶኖች (ውስጣቸው የሚይታዩ ብልቃጦች፣ የውሃ መያዣ ላስቲኮች) በማዘጋጀት በእያንዳንዱ ውስጥ ጤና አዳም፣ የባሕር ዛፍ ቅጠል፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ሣሙና የመሳሰሉትን ሽታ ያላቸውን ነገሮች በመክተት አነስተኛ ቀዳዳ በማበጀትና ሕጻናቱ በቀዳዳው በኩል እያንዳንዱን እንዲያሽቱ በማድረግ ውስጥ ያለውን ሽታ እንዲለዩ ማድረግ

በመቅመስ እንወቅ



* ምግብ ከተመገብን በኋላ ሕጻናትን ዓይናቸውን በጨርቅ በመሸፈን ከዚያም ምላሳቸው ላይ በየተራ ስኳር፣ ጨው ፣ እንዲሁም ከተመገቡት የምግብ አይነት ውስጥ (ለምሳሌ እንጀራ፣ ዳቦ፣ ሽሮ ወጥ፣ ወዘተ.) በማድረግ እንዲቀምሱና ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

* በየቤቱ የሚገኙ እንደ ማበጠሪያ፣ እርሳስ፣ ማንኪያ፣ ኩባያ፣ ኳስና የመሳሰሉትን በከረጢት ውስጥ መጨመርና ሕጻናት በከረጢት ውስጥ እጃቸውን በመክተት አንዱን ዕቃ በእጃቸው እንዲጨብጡና ሳያወጡት የዕቃውን ሰም መናገር፣ በመቀጠልም ካወጡት ብኃላ ስለዕቃው ምንነት እንዲናገሩ ማድረግ



ምርምር

* ደረቅ ባቄላ እንዲሁም ንጹህ ከዳን ያለው የውሃ ላስቲክ ማዘጋጀትና ለሕጻናት ባቄላውን በመስጠት ስሙን መጠየቅና መንገር፤ በተዘጋጀውም የውሃ ላስቲክ ውስጥ ንጹህ ውሃ በመጨመር ሕጻናት የያዙትን ደረቅ ባቄላ ጣሳው ውስጥ እንዲጨምሩት ማድረግ። በሁለተኛው ቀን ለሕጻናት የራሰውን ባቄላ ከጣሳው ውስጥ በማውጣት መስጠትና በእጃቸው እንዲፈትሹት ማድረግና ከቀደመው ባቄላ አንጻር ያለውን ለውጥ መጠይቅ፤ በመቀጠልም የራሰውን ጥሬ ባቄላ በደረቅ ጣሳ ውስጥ ከድኖ ማስቀመጥና በሦስተኛው ቀን ከፍቶ የጎነፈለውን ባቄላ እንዲመለከቱና ያዩትን ለውጥ መጠየቅ። በመጨረሻም በሕጻኑ ስም ጣሳ ማዘጋጀትና አፈር በመሙላት የጎነፈለውን ባቄላ መትከልና በየጊዜው ውሃ እያጠጡ እድገቱንና ለውጡን እንዲከታተሉ ማድረግ

ከመጫወታችን በፊት እንዲሁም ከተጫወትን በኋላ እጆቻችንን በውሃና በሳሙና እንታጠብ ፣ ሕጻናትም እጆቻቸውን እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው እናሳያቸው ፣ እናግዛቸው

ተረት ተረት አውቃለሁ፣ መዝሙር እዘምራለሁ፣ የእቃዎችን ስም አውቃለሁ!




* ከሕጻናት አቅም ጋር የተመጣጠነ አጭር ተረትን መተረክ፣ ቀላል ዐረፍተ ነገሮችን መጠቀም (በቤት ውስጥ የሚገኝ ከሆነም በስዕል ማስደገፍ) እና እንደየአስፈላጊነቱ በየመሀሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ተረቶቹን ሲተርኩ ሕጻናቱ የተራኪውን የፊት ገጽታ እና አካላዊ እንቅስቃሴ መከታተል በሚችሉበት ቦታ አቀማመጣቸውን በማድረግ ተረቱን መተረክ ያስፈልጋል

* ሕጻናቱን አጫጭር መዝሙሮችን መዘመርና እንዲያደምጡ ማድረግ፣ ሕጻናትም ከእንቅስቃሴ ጋር እንዲዘምሩ ማድረግ፤ በተጨማሪም ወላጆች/አሳዳጊዎች መዝሙሮቹን ለሕጻናቱ ካስጠኗቸው ብኃላ የመዝሙሮቹ መልዕክት ምን እንደሆነ መጠየቅ

* በአንድ በኩል ክፍት የሆነ ከፍ ያለ ካርቶን ከሕጻናቱ ፊት በሚገኝ ጠረጴዛ ላይ በማድረግ ክፍቱን ጎን ወደ ወላጆች/አሳዳጊዎች ድፍኑን ደግሞ ወደሕጻናቱ ማድረግ፤ ከካርቶኑም ጀርባ ሕጻናቱ እንዲያዩት ኳስ፣ ጨርቅ፣ ኩባያ፣ አሻንጉሊት፣ እንጨት፣ ሳህንና የመሳሰሉትን ማስቀመጥ፤ በፊት ለፊት ባለው ክፍት ጎንና በሕጻናቱ በኩል ባለው ትንሽ የእጅ ማሹለኪያ ማበጀትና ወላጆች/አሳዳጊዎች “እጄ ባዶ ነው እጄ ኳስ ይፈልጋል” ሲሉ ሕጻናቱ እየተነሱ የተጠየቀውን ዕቃ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማስያዝ። በዚህም መሠረት ሁሉም ዕቃዎች በወላጆች/አሳዳጊዎች እጅ እስከሚሆኑ ድረስ ጨዋታውን መቀጠል፣ በተጨማሪም ሕጻናቱና ወላጆች/አሳዳጊዎች ቦታቸውን በመቀያየር ጨዋታውን መጫወትና በዚህም አማካኝነት የዕቃዎችን ስሞች እንዲለዩ ማድረግ።

ከመጫወታችን በፊት እንዲሁም ከተጫወትን በኋላ እጆቻችንን በውሃና በሳሙና እንታጠብ ፣ ሕጻናትም እጆቻቸውን እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው እናሳያቸው ፣ እናግዛቸው



በክሮች መጫወት

* ሰፋፊ ቀዳዳ ያላቸውን ቆርኪዎች፣ ፕላስቲክ ክዳኖችና የመሳሰሉትን በመጠቀም በቀዳዳው ውስጥ ክር እንዴት ማስገባት እንደሚቻል ማሳየትና ለሕጻናቱ እነዚህን በማቅረብ በቀዳዳው ውስጥ ክሮቹን ማስገባት እንዲለማመዱ ማበረታታት።

* ወፍራም ካርቶን በተለያየ ቅርጽ በመቁረጥ በእያንዳንዱ መሃል ሰፊ ቀዳዳ ማበጀትና የተቆራረጡትን ካርቶኖች ከክሮቹ ጋር ለሕጻናቱ መስጠት። በመቀጠልም ሕጻናቱ ከቦቹን፣ ጎነ ሦስቶቹንና ካሬዎቹን ለየብቻ በመምረጥና በመለየት በቀዳዳው ውስጥ ክር እያስገቡ እንዲጫወቱ ማለማመድ።

* ለሕጻናቱ የተለያዩ ቁርጥራጭ ክሮችን በመስጠት መቋጠርን እና መቀጠልን እንዲለማመዱ ማድረግ

ከመጫወታችን በፊት እንዲሁም ከተጫወትን በኋላ እቆታችንን በውሃና በሳሙና እንታጠብ ፣ ሕጻናትም እቆታቸውን እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው እናሳያቸው ፣ እናግዛቸው



ማዛመድና ማስታወስ

* ሰፋ ያለ ካርቶን ውስጥ ተመሳሳይ ዓይነት ነገሮችን በጥንድ መክተትና እያንዳንዱን ከመሃከል እያወጡ ማሳየትና ተመሳሳይ የሆነውን ሕጻናት በየተራ ፈልገው እንዲያወጡ፤ ለምሳሌ ጥንድ እርሳሶችን፣ ጥራጥሬ ፣ ቆርኪና የመሳሰሉትን መጠቀም

* የጎደለውን ፈልግ - በጠረጴዛ ላይ ከ 3 ያልበለጡ የተለያዩ ነገሮችን በማስቀመጥ ሕጻናቱ እንዲያስተውሉ ማድረግ። በመቀጠልም ሕጻናቱ ዓይናቸውን እንዲጨፍኑ ወይም ፊታቸውን አዙረው እንዲቆሙ በማድረግ አንዱን ነገር ማንሳትና የጎደለውን አስተውሰው እንዲናገሩ መጠየቅ፣ ሕጻናቱ ለመናገር የሚከብዳቸው ከሆነ ጠረጴዛው ላይ ምን ምን ነበር? በማለት ያለውን አብሮ መጥራት

* ሕጻናትን ዓይናቸውን በመሸፈን የክብ፣ ካሬና ሦስት ማዕዘን ቅርጾችን በመስጠት ዓይናቸው እንደተሸፈነ እንዲለዩአቸው ማድረግ

* የተለያዩ እህሎችን/ጥራጥሬዎችን (ለምሳሌ ሽምብራ፣ ገብስ፣ ስንዴ፣ በቆሎና የመሳሰሉትን) መቀላቀል፤ በመቀጠልም ሕጻናቱን እንዲዘግኑ ማድረግና ለእያንዳንዱ እህል ባዶ እቃዎችን በማስቀመጥ እህሎቹን በዓይነታቸው እንዲያስቀምጡ ማድረግ

ከመጫወታችን በፊት እንዲሁም ከተጫወትን በኋላ እቆታችንን በውሃና በሳሙና እንታጠብ ፣ ሕጻናትም እቆታቸውን እንዴት መታጠብ እንዳለባቸው እናሳያቸው ፣ እናግዛቸው

ቤታችን

ውስጥ ሆነን እንጫወት



ChildFund®